# ልደታ ክፍለከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት የ6ኛ ክፍል የግብረገብ ትምህርት ሞዴል ፈተና 2016ዓ.ም

**የጥያቄ ብዛት: 40** **የተፈቀደው ሰዓት: - 1 ሰዓት**

## አጠቃላይ ትዕዛዝ

የግብረገብ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ እያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡

መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙስ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጸዳት አለበት፡፡

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡ ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

## I. ለሚከተሉት ጥያቃዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ በተሰጠው መልስ መስጫ ላይ ፃፉ

1 የግብረገብ ምሉእነትን የተላበሱ ሰዎች ከሚከተሉት አንዱ ባህሪ ሊኖራቸው አይገባም፡፡

ሀ. ወጥነት ሐ. ሀላፊነት የሚሰማቸው

ለ. ሀቀኝነት የጎደለው መ. ድፍረት መኖር

2. የመልካም እሴት መገለጫ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ.የተቸገሩን መርዳት ሐ. ታማኝነት

ለ. ስለሌሎች ማሰብ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3 .ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዢ የሆኑ ዜጎችን የሚገልጸው የቱ ነው?

ሀ. ለሙስና የተጋለጡ ናቸው ሐ. መብትና ግዴታቸውን ያውቃሉ

ለ. ሀላፊነታቸውን በአግባቡ አይወጡም መ.መብታቸውን ብቻ ያስከብራሉ

4. በግብረገብ ምሉእነት ራሳቸውን የሚመሩ ሰዎች ያሉት ማህበረሰብ የሚያገኘው ጥቅም የቱ ነው?

ሀ. በሌሎች ልፋትና ድካም ጥቅም ማግኘት ሐ. የማህበራዊ ግንኙነታቸው ጠንካራ አለመሆን

ለ. ጠንካራ የስራ ባህል አላቸው መ.ራሳቸውን ከሌሎች አስበልጠው ማየት

5. ከሚከተሉት ሀላፊነት መሰማትን የሚገልፀው ሀሳብ የትኛው ነው?

ሀ. የኤች. አይ .ቪ. ኤድስ ህሙማንን ማግለል ሐ.ስልጣንን ለግል ጥቅም ማዋል

ለ. ቆሻሻን በየትኛውም ቦታ ማስወገድ መ.የህፃናትን ጥቃት በዝምታ አለመመልከት

6. የግብረገብ ምሉእነት ማህበራዊ ትስስራችንን የሚያጠናክርልን

ሀ. ራሳችንን ከሌሎች በማሳነስ ሐ.ተለዋዋጭ ባህሪን ስንላበስ

ለ. በሰዎች ዘንድ እምነት ሲጣልብን መ. ስለሌሎች ባለማሰብ

7.ስህተታቸውን የሚያምኑ ሰዎች የሚገለፁት በ……………………….ነው?

ሀ.ርህራሄ ለ. ድፍረት ሐ.ሀቀኝነት መ. ሀላፊነት

8…………ትክክል ነው ብለን ያመንበትን ነገር እንድንተገብር የሚያስችል ውስጣዊ ችሎታ ነው

ሀ.ህግ ሐ.ወጥነት

ለ.ድፍረት መ.ርህራሄ

9…………ከመሰረታዊ እሴቶች ጋር የመኖር ችሎታ ነው

ሀ.ምሉዕነት ሐ.ሀላፊነት መቀበል

ለ.ተጠያቂነት መ.ለራስ ብቻ ማሰብ

10. የተቸገሩን መርዳት ፣የታመሙን መጠየቅና አረጋዊያንን መንከባከብ የሚገልፀው የትኛው ነው?

ሀ.ርህራሄ ሐ. ስለ ሌሎች በማሰብ

ለ. ሀላፊነትን በመወጣት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

11. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቃልን መፈፀም ታማኝነት ነው ሐ. ድፍረት የምሉዕነት መገለጫ አይሆንም

ለ.በራስ መተማመን ምሉዕነት ነው መ. የሌሎችን ሰዎች ችግር መረዳት መቻል

12. ከሚከተሉት ውስጥ የተማሪዎች ስነ-ምግባር መሆን ያለበት የትኛው ነው ?

ሀ.በራስ መተማመን ሐ.ሀላፊነትን መወጣት

ለ. ስለ ሌሎች ማሰብ መ.ሁሉም መልስ ናቸው

13. ህይወትን በግብረገብ ምሉዕነት ለመምራት አስፈላጊ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ.ስህተቶችን አይቶ ማለፍ ሐ.ተግባርን መገምገም

ለ.ለራስ ክብር መስጠት መ.ሀላፊነትን በአግባቡ መወጣት

14.ለህግ ተገዥ አለመሆን ከሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች ውስጥ አንዱ የትኛው ነው?

ሀ.የሰብአዊ መብቶች መጠበቅ ሐ. የሰላም እጦት

ለ.የዜጎች ነፃነት መከበር መ. የህግ መከበር

15.ስልጣንን ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ ጓደኛ(ዘመድን) ለመጥቀም የሚፈፀም የሙስና አይነት የትኛው ነው?

ሀ.የዝምድና ወገንተኝነት ሐ.ማጭበርበር

ለ. ጉቦ መስጠት መ.መልስ የለም

16. አንድ ሀገር ከጣልቃገብነት ነፃ ሆና ራሷን በራሷ ማስተዳደሯ የሚገለፀው በ……..ነው?

ሀ. ገለልተኛ ለ. ሉዓላዊነት ሐ.ህግ መ.ቅኝ መገዛት

17.ህጎች በሀገር ደረጃ ሲወጡ ማሟላት ካለባቸው መስፈርቶች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. ቋሚ ህግ ሐተለዋዋጭ ህግ

ለ. ወጥነት ያለው ህግ መ. መልስ የለም

18.በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ ሀብቶችን እኩል የመጠቀም መብት የሚገልፀው የቱ ነው?

ሀ.ግዴታን በመወጣት ሐ. ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል

ለ.በሉዓላዊነት መ. ነፃነት

19. ……..በአንድ ሀገር ውስጥ የትኛውም ሰው ሊከተለው የሚገባ የስነ-ምግባር ህግ ነው?

ሀ.መብት ሐ.ነፃነት ማግኘት

ለ.ሀላፊነት መውሰድ መ. ህግ

20. ማህበረሰቡ ከጊዜ ብዛት የሚለውጠው የህግ ዓይነት የትኛው ነው?

ሀ. ተለዋዋጭ ህግ ሐ. ወጥነት ያለው ህግ

ለ. ቋሚ ህግ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

21. ህጻናትን ለአስገዳጅ ስራ ማሰማራትን የሚገልጸው የቱ ነው?

ሀ. የህጻናት መብት እና ግዴታ ሐ. የህጻናት የህግ ጥበቃ

ለ. ህገ ወጥ የህጻናት ዝውውር መ. የህግ ተገዥነት

22. ሰው ሆነን በመፈጠራችን የምናገኘው የመብት ዓይነት የትኛው ነው?

ሀ. የኃይማኖት መብት ሐ. ማህበራዊ ግንኙነት

ለ. ለህግ ተገዥነት መ. ሰብዓዊ መብት

23. ከሚከተሉት አደንዛዥ እጾች የሆኑና በጤና ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት የሚገልጹት የትኞቹ ናቸው

ሀ. አካልና አእምሮን ይጎዳሉ ሐ. ማህበራዊ ህይወትን ያበላሻሉ

ለ. አልኮል፣ጫትና ሲጋራን ያካትታሉ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

24. ከሚከተሉት በህጻናት ላይ አካላዊና ስነልቦናዊ ተጽዕኖ የሚፈጥረው የትኛው ነው?

ሀ. የቤተሰብ ፍቅር ማጣት ሐ. የህጻናት መብቶች መከበር

ለ. የመሰረታዊ ፍላጎቶች መሟላት መ. ለህጻናት ፍቅር መስጠት

25.ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዥነት ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. ሰላምን መጠበቅ ሐ. ነጻነትን ማጣት

ለ. የዜጎች ፍላጎት መጠበቅ መ. ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል መኖር

26. ለሰዎች ህይወትና አካል ደህንነት ስጋት የሚሆነው የመብት ጥሰት የትኛው ነው?

ሀ. የሰብአዊ መብት ጥሰት ሐ. የዲሞክራሲ መብት ጥሰት

ለ. የኃይማኖት መብት ጥሰት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

27. ከሚከተሉት ውስጥ ጥሩ ባህሪ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ክብር መስጠትና እንግዳ ተቀባይነት ሐ. የመምህራንን ትእዛዝ መፈጸም

ለ. የገቡትን ቃል አለማክበር መ. እንግዶችን በወዳጅነት ስሜት ማየት

28. ከሚከተሉት ውስጥ የሁሉም ኢትዮጵያውያን የግብረገብ እሴት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ለወላጆች ተገቢውን ክብር አለመስጠት ሐ. ለአረጋውያን ክብር መስጠት

ለ. እንግዳን በተገቢው መንገድ አለመቀበል መ. አለመከባበር

29. ከሚከተሉት መካከል መልካም ባህሪን ለማሳደግ የማያስችለን የትኛው ነው?

ሀ. ራስን አለመቆጣጠር

ለ. የማህበረሰባችንን የግብረገብ ስነልቦና ከግምት ውስጥ ማስገባት

ሐ. የትምህርት ቤት ህግና ደንቦችን ማክበር

መ. ታማኝ መሆን

30. ከሚከተሉት መካከል የትምህርት ቤት ህግና ደንብ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. በሰዓቱ አለመድረስና አርፍዶ ትምህርት ቤት መምጣት

ለ. የትምህርት ቤቱን የደንብ ልብስ በአግባቡ አለመልበስ

ሐ. ለብሔራዊ መዝሙርና ለሰንደቅ ዓላማ ክብር መስጠት

መ. የትምህርት ቤቱን ንብረት አለመጠበቅ

31. ለሌሎች ክብር መስጠትን የማይገልጸው የትኛው ነው?

ሀ. ለሌሎች ሰዎች ንብረት እውቅና መስጠት

ለ. ሌሎችን እንደራስ መመልከት

ሐ. ለሌሎች አድናቆት መስጠት

መ. ለራስ ቅድሚያ መስጠት

32. ራስን መቆጣጠር የአንድን ሰው የህይወት ስኬት ሊገልጽ የሚችለው እንዴት ነው?

ሀ. መጥፎ ባህሪያትን መቋቋም አይቻለውም ሐ. ፍላጎቱን፣ስሜቱንና ልምዶቹን አይቆጣጠርም

ለ. ራሱን አደብ የሚያስገዛበት ችሎታ ነው መ. ሃሳቡን፣ ምኞቱንና ልምዶቹን አለመቆጣጠር

33. ¨ከሚከተሉት ውስጥ የመልካም ባህሪ ምሳሌዎች ከሆኑት ወስጥ የሚካተተው የቱ ነው?

ሀ. ትክክል ለሆነው ነገር አለመወገን ሐ. ጠንካራ ሰራተኞችን አለማድነቅ

ለ. ለሰሩት ስህተት ይቅርታ አለመጠየቅ መ በራስ መተማመን

34.በተማሪዎች ላይ የሚታይ መልካም ያልሆነ ባህሪ የቱ ነው?

ሀ.ፈተናን መኮረጅ ሐ. ታማኝ መሆን

ለ. አለመዋሸት መ.የትምህርት ቤት ንብረት መጠበቅ

35. ለመልካም ባህሪ መቀረጽ ምክንያት የማይሆነው የቱ ነው?

ሀ.ቤተሰብ ሐ.ምርጫ

ለ. የጊዜ ቆይታ(አካባቢ) መ. መልስ የለም

36.በህግ መሰረት አንድ ሰው ህፃን የሚባልበት የእድሜ ክልልን የሚገልፀው የትኛው ነው?

ሀ. ከ5 አመት በታች ብቻ ሐ. 10 አመት ሲሞላው

ለ.እስከ 18 አመት ድረስ መ.ከ 18 አመት በላይ

37. የልጆችን ስነ ምግባር ለማነፅ አስተዋፅኦ የሌለው የትኛው ነው?

ሀ.ቤተሰብ ሐ. አካባቢ

ለ. ትምህርት ቤት መ. የጤና ተቋም

38. ከሚከተሉት ውስጥ የሙስና ተግባር ያልሆነውን የሚገልፀው የቱ ነው?

ሀ.መደለያ ጉቦ መቀበል ሐ. ሚስጥር መጠበቅ

ለ.የመንግስትን ንብረት ለግል ጥቅም መዋል መ. ማጭበርበር

39.ግብር ላለመክፈል የሚደረግ ህገ-ወጥ ተግባር ምን ተብሎ ይጠራል ?

ሀ. የፍትህ እጦት ሐ..የሰላም እጦት

ለ. የመብት ጥሰት መ. ግብር ስወራ

40. ከሚከተሉት ውስጥ የሉዓላዊነት መገለጫ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ.ህዝብ ሐ.የነፃነት እጦት

ለ. መንግስት መ.ድንበር